# በታማኝ በየነ እና አምባሳደሩ መካከል የነበረው አለመግባባት
# በኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ እይታ
## ጌታቸው ረዳ
## (Ethiopian Semay)

ባለፈው ወር አብይ አሕመድ ወደ አሜሪካ በመምጣት ኢትዮጵያውያንን ለማነጋጋር በተካሄደው ዝግጅት በሚመለከት ጉዳይ በኢትዮጵያ የወያኔ/ኢሕአዴግ የዋሺንገተን ዲሲ አምባሲ አምባሳደር በከያኒ ታማኝ በየነ ላይ ‘ሴራ’ በመጎንጎን መድረክ እንደነፈጉት ተደርጎ እራሱ ታማኝ በየነ በኢሳት ቴ/ቪዥን ቀርቦ የሰጠው የራሱን ምላሽ ሰምተነዋል። ብዙ ሰዎች እኔም ጨምሮ ታማኝ በተናገረው ቅሬታ ወደ ማመን ሄጄ ነበር (እስከ ዛሬዋ ድረስ የመልስ መልስ ስላላደመጥን)። ዛሬ የአምባሳደሩን መልስ የቪ ኦ ኤዋ የአማርኛ ክፍል ጋዜጠኛ ጽዮን ግርማ ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅ ካደመጥኩኝ በኋላ ግን የአምባሳደሩ ስም በውሸት እንዲጠቁር መደረጉ በጣም ስሕተት ነበር። ስለዚህ ይህንን ቃለ መጠይቅ ካደመጣችሁ በኋላ በአምባሳደሩ ላይ የነበራችሁ የተሳሳተ እይታ ያላችሁ ሰዎች ካላችሁ ዕይታችሁን አስተካክሉ። ከታች የምሰጣችሁ መረጃ ከቀረበላችሁ በኋላ የሰው ስም በከንቱ በማጥፋት ላይ ችክ የምትሉ ሱሰኞች ካላችሁም አደብ ግዙ።

ይህን ስላልኩኝ ደግሞ እንደ አመላችሁ ጌታቸው ረዳ አምባሲው ጋር መሞዳሞድ ጀመረ እንዳትሉ ያው በዚያ አንደማልታማ የምታውቁ ይመስለኛል። ምድረ አሽቃባጭ ስትደመር አሁንም ገና ነኝ አልተደምርኩም፡ ስለዚህ አምባሳደሩን ልቀቁት። ታማኝ በየነ የመድረክ አዘጋጅ እንዲሆን ያልተደረገበት ምክንያት ከአገር ቤት የተመደበ ሰው ስለነበረ (ዳንኤል ክብረት ለማለት ይመስለኛል) እንጂ ታማኝን በማግለል አይደለም ብሏል አምባሳደሩ በቅንነት። ሁኔታው ከአምባሳደሩ የሰው መዳቢነት ሥልጣን በላይ ነው ማለት ነው። እኔም በዚህ አምባሳደሩን አምኜዋለሁ። ለማንኛውም ይህንን ቃለ መጠይቅ አድምጡ እና ሰውን ማመንዠኩን አቁሙ (አሁንም በየ ዩቱቡ ላይ እንደ ምጣድ ተጥደው በዚህ ጉዳይ የሚቃዡ ስላስተዋልኩ ነው ይህንን መረጃ የሰጠሁዋችሁ። የምቃወመው ሰውም ቢሆን ሰው በከንቱ ስሙ ሲጎድፍ ያበሳጨኛል፡ አልወድም! ዶ/ር ፍስሃ እሸቱ በሚያሰራጨው የፖለቲካ እቃወመው ነበር ፤ የዲሲ ግብረሃይል የተባለ የጋንግ/mob/ ቡድን “ያለፈቃዱ በቁጥጥር ስር አውለነዋል/Involuntary Imprisonment/” ብለው በሕዝብ ፊት ሲያስሩትና ሲሰድቡት የተሰማኝ ንዴት በወቅቱ በጽሑፍ ገልጫለሁ። አሁንም በዚህ መልክ የምንቃወማቸው ሰዎች ላይ በሓሰት ስማቸው ሲጠቁር እውነታውን ፈልጎ ማወቅ ያስፈልጋል።

Ethiopia: ጽዮን ግርማ አምባሳደር ካሳን አፋጠጠቻቸው

https://youtu.be/j6bdpFT7AnQ

ጌታቸው ረዳ (Editor - Ethiopian Semay)